# የተዳፈነ እሳት

በወርሃ ግንቦት፣ የተቀጣጠለው
የዴሞክረሲ እሳት፣ የሚንቀለቀለው
የወያኔን ጎራ፣ ያተረማመሰው
በአጋዚ ጥይት፣ ቢመስል የጠፋ
ጋደም አለ እንጂ፣ መቸ አንቀላፋ!

የነፃነት እሳት፣ ያርበደበዳቸው
የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ቁጣ ያስደነገጣቸው
የሞት ሽረት ትግል፣ ሆነና ምርጫቸው
ንፁሃን ዜጎችን፣ ቢገድሉና ቢያስሩ
መርዛም ስራቸውን፣ ቢረጩ፣ ቢዘሩ
እውነትና ሐቅን፣ አይችሉም ሊቀብሩ
ህሊና ካላቸው፣ ከታሪክ ይማሩ፡፡

የነፃነት እሳት፣ አንዴ ከነደደ
ሊጠፋ አይችልም፣ አልሚን ካልወለደ፡፡

ባምባገነን መሪ፣ በጠባብ ዘረኛ
በውሸታም ከሀዲ፣ ሆድአደር ቅጥረኛ
ኢትዮጵያ አትገዛም፣ ሞተን ሳናልቅ እኛ፡፡

ወንዙ ሀይቁ ሞልቶ፣ ውሃ ስንጠማ
በለምለም አፈር ላይ፣ ዳቦ ስንሻማ
ምነው ዘዴ ጠፋ፣ ለኛ የሚስማማ?

ቤታችንን ለቀን፣ የሰው ቤት ስንጠና
ጉዳችንን ችለን፣ ሽፍነን ገበና
ልመናችን በዝቶ፣ ችግራችን ከሮ
እየደበደብን፣ የቅሌት ከበሮ
ዘላለም መከራ፣ ዘላለም ዕሮሮ
መሞት ይሻለናል፣ ከዚህ አይነት ኑሮ፡፡

የተዳፈነው እሳት፣ መጨሱ መች ቀረ
አመድ ሆኖ አልቀረ፣ እንደተቀበረ
ብረዛው፣ አፈናው፣ ብተናው፣ ቢከፋ
መንደዱ አይቀርም፣ አትቁረጡ ተስፋ፡፡

ኢትዮጵያዊው እሳት፣ እንደገና ሲነድ
አጥፊውን ማገዶ፣ የደርገዋል አመድ፡፡

ተዳፈነ እንጂ፣ አልጠፋም እሳቱ
ይለቀም ቅጠሉ፣ ይፈለጥ እንጨቱ
ቆስቆስ ቆስቆስ አርጉት፣ ወገኖቼ በርቱ
በነፃነት ብርሃን፣ እንዲነጋ ሌቱ
ለመቸ ሊሆን ነው፣ ኢትዮጵያዊነቱ፡፡

(ከሣህሉ በቀለ ቶሮንቶ)